**CEC**
100 Galena Street
Aurora, CO 80017
(720) 338-7860

Colorado Ethiopian Community Edir
**7th October 2017**

መግቢያ፦

በሀገራችን በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን እንደሚሰራበት የአንድ አካባቢ ነዋሪ ሕዝብ እርስበርሱ በማህበር(በዕድር) ተደራጅቶ በሞት ጊዜ ለቀብር ሲረዳዳ መቆየቱ ይታወሳል።እኛም በኮሎራዶ ስቴት በዴንቨር ከተማና አካባቢው የምንኖር ኢትዮጵያውያንና ትውልደ -ኢትዮጵያውያን ይህንኑ የሀገራችንን የመረዳዳት መልካም ባህል በመከተል : የማህበሩ አባል ወይም ቤተሰብ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የቀብር ሥነ-ስርዓት ወጪን ለመሸፈን የሚረዳ ቀጥሎ በተመለከተው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መረዳጃ ማህበር (ዕድር) አቋቁመናል።

**አንቀጽ አንድ፦** መጠሪያ ስም........

1.1 በኮሎራዶ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ መረዳጃ ማህበር (እድር) ተብሎ ይጠራል።

**አንቀጽ ሁለት፦** የማህበሩ አድራሻ........

2.1 የማህበሩ አድራሻ በኮሎራዶ ስቴት በዴንቨር ከተማና አካባቢው ሲሆን ፤ጊዜያዊ አድራሻው በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ጽህፈት ቤት የሚገኝበት 1532 ጋለና መንገድ ቢሮ ቁጥር 100 አውሮራ ኮሎ 80010 ነው።

**አንቀጽ ሶስት፦** ዓላማ

3:1 ማህበሩ በአሜሪካ የሀገር ውስጥ ገቢ ህግ (U.S.Internal Revenue Code 501 3 C ) ለትርፍ ያልተቋቋመ ፤ከማንኛውም ፖለቲካ ፤ ሃይማኖት ፤እና ዘር ገለልተኛ የሆነ ፤ ኢትዮጵያዊነትን ብቻ መሠረት ያደረገ ሲሆን ፤ ዓላማው ፦ አንድ አባል ወይም ቤተሰቡ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለቀብር ማስፈፀሚያ ወይም አስከሬኑን ወደ ኢትዮጵያ ለመላኪያ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ በማድረግ እርስ በርስ ለመረዳዳት ነው።

3:2 አባላት በቀብር ስነ ስርአት ላይ እንዲገኙ፣ በባህላችን መሰረት ለቅሶ በመድረስ እንዲያስተዛዝኑ መንገርና ማስተባበር፦

3:3 የማህበሩ አባላት ስለአስተማማኝ ኢንሹራንስና የቁም ኑዛዜ የግንዛቤ ትምህርት አቅም በፈቀደ መልኩ መስጠት::

3:4 ለወደፊት ለማህበሩ አባላት ጥቅም ያስገኛል ተብሎ የሚታመንበትን ማንኛውንም ዓላማ እንደ አስፈላጊነቱ በእቅድና በአባላቱ ውሳኔ መሰረት ስራ ላይ ማዋል።

## አንቀጽ አራት፦ ትርጓሜ

4፡1 ማህበር ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት፦ በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ (ኮሙኒቲ) በሞት ጊዜ በጋራ ለመረዳዳት ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበራዊ ድርጅት ማለት ነው።

4፡2 አባል ማለት፦በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ መረዳጃ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በአባልነት የተመዘገበና የአባልነት ግዴታውን የፈፀመና በመፈጸም ላይ ያለ አባል ማለት ነው።

4፡3 ቤተሰብ ማለት፦የማህበሩ አባል የሆኑ ባልና ሚስት ፤ እድሜያቸው ከ18 አመት ያልበለጡ ወይም( በኮሌጅ/ በዩኒቨርሲቲ በመማር ላይ ያሉ እድሜያቸው ከ23 አመት ያልበለጡ) ፤በአባል ቤተሰብ የሚረዱና ከአባሉ ጋር የሚኖሩ ልጆች ማለት ነው።

4፡4 ልጆች ማለት፦ከአባሉ አብራክ የተወለዱ፤በህጋዊ ማደጎ ወይም ጉዲፈቻ የተገኙ ፤እድሜያቸው ከ18 አመት ያልበለጡ ወይም የኮሌጅ /ዩኒቨርሲት ተማሪ ሆነው እድሜያቸው ከ23 አመት ያልበለጡና፤ በወላጆች ድጋፍ አብሮ የሚኖሩ የጋራ ልጆች፤ የባል ወይም የሚስት ልጆች ወይም በህመም (በበሽታ) ምክንያት ወይም አካለ ስንኩል ሆነው የቤተሰብ ጥገኛ ሆነው እድሜያቸው ከ18 አመት በላይ የሆኑ ማለት ነው።

4፡5 በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው ለሴት ፆታም ያገለግላል።

## አንቀጽ አምስት፦ አባልነት

5፡1 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፤ ትውልደ-ኢትዮጵያዊ ዕድሜው ከ18 አመት በላይ የሆነ፤ በኮሎራዶ ስቴት በዴንቨር ከተማና አካባቢው ነዋሪ የሆነ፤ የማህበሩን መተዳደሪ ደንብ የተቀበለ፤ በፈቃደኝነት የማህበሩ አባል ለመሆን ማመልከቻ ሞልቶ ያቀረበ ፣ማህበሩ የሃይማኖት ፤የዘር፤የፃታ፤ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ሳያደርግ በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ በአባልነት ተቀብሎ ይመዘግባል ።

5፡2 የመረዳጃ ማህበሩ አባል ለመሆን ፤ በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ድርጅት አባል መሆን ጠቃሚና አስፈላጊም ነው።
የእድር አባል ሆኖ የኮሙኒቲ አባል ያልሆነ ሰው የቢሮ ኪራይና ሌሎች ወጭዎችን ለመሸፈን የአገልግሎት (service) $3.00 በወር ይከፍላል።

አንቀጽ ስድስት ፦ መዋጮ ፤ግዴታና መብት፦

6፡1 አንድ የመረዳጃ ማህበሩ አባል ለመሆን የሚፈልግ ሰው ለአባልነት የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ በመፈረም ያመለክታል።ባለትዳር ከሆኑና 18 ዓመት እድሜ ያልበለጡ ልጆቻቸውን በመዘርዘር ከባለቤቱ ጋር ቅጹን በመሙላትና በጋራ በመፈረም አባል ለመሆን ያመለክታሉ።

6፡2 የአባልነት ክፍያና ወርሃዊ መዋጮ፦

**ሀ/ የአባልነት መመዝገቢያ ( ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚከፍል )**

6፡2፡1 ባለትዳርና ልጆች ያላቸው ቤተሰብ የአባልነት መመዝገቢያ. $250.00

| | |
|---|---|
| ባለትዳር ሆነው ልጆች የሌላቸው.. ........... | $200.00 |
| ልጆች ኖሯቸው ትዳር የሌላቸው.. .............. | $150.00 |
| ትዳር የሌለው ብቸኛ ሰው......................... | $100.00 |

**ለ/ ወርሃዊ መዋጮ (የየውሩ ታስቦ በየ 6 ወሩ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከፈል)**

| | |
|---|---|
| ባለትዳርና ልጆች ያላቸው በወር.. ................ | $20.00 |
| ባለትዳር ሆነው ልጆች የሌላቸው.. ................ | $15.00 |
| ልጆች ኖሯቸው ትዳር የሌላቸው.. .................. | $15.00 |
| ትዳር የሌለው ብቸኛ ሰው.............................. | $10.00 |

6፡3 በወላጆቻቸው ጥገኝነት ስር ተመዝግበው የነበሩት ልጆች ከ18 ዓመት እድሜ በኋላ የመመዝገቢ መዋጮ ሳይከፍሉ በግንባር ቅጽ ሞልተው በመመዝገብ ወርሃዊ መዋጮውን ብቻ በመክፈል አባል ሆነው መቀጠል ይችላሉ።

6፡4 ባለትዳር የነበሩ ህጋዊ የትዳር ፍቺ ካደረጉ ሁለቱም ሕጋዊ የትዳር ፍቺያቸውን በማቅረብ የመመዝገቢያ መዋጮ ሳይከፍሉ በየግንባራቸው ቅጽ ሞልተው ወርሃዊ መዋጮ በየግንባር እየከፈሉ አባል ሆነው መቀጠል ይችላሉ።

6፡5 የማህበሩ አባል የነበረ ሰው አዲስ ትዳር ሲይዝ ከትዳር ጓደኛው ጋር የጋብቻ ማስረጃቸውን አቅርበው አባል ያልነበረው ወገን ከላይ ከተተመነውን የባለትዳር $200.00 የድርሻውን $100.00 የመመዝገቢያና ወርሃዊ መዋጮ በመክፈል በባለትዳር ተመዝግበው አባል ይሆናሉ።

## አንቀጽ ሰባት፦የአባልነት ግዴታ ፦

7፡1የመረዳጃ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማክበርና መተግበር፤ የየወሩ ታስቦ በየ6 ወሩ የሚከፈለውን የማህበሩን ወርሃዊ መዋጮ በወቅቱ መክፈል

7፡2 አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በስብሰባ ላይ መገኘት ፤ በአባል የቀብር ስነሥርአት ላይ መገኘት፤ወይም ወደ ሀገር ቤት አስከሬን ሽኝት ላይ በመገኘትና፤ ሀዘን የደረሰበትን ቤተሰብ ማስተዛዘን ይጠበቅበታል።

7፡3 አባል ወይም የአባል ቤተሰብ በሞት ከተለየ ፤ ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቅ የቤተሰብ አባል ለማህበሩ አመራር በወቅቱ ማሳወቅ።

7፡5 የማህበሩ አባል ወይም የአባል ቤተሰብ ሁኔታ ከተለወጠ(ለምሳሌ የልጅ እድሜ 18 አመት ሲጨርስ ፤ ልጅ ሲወለድ፤የጋብቻ ፍቺ ሲደረግ፤አዲስ ጋብቻ ሲፈጸም፤ከ18 አመት በታች የሆነ ልጅ ከሀገር ቤት መጥቶ ከወላጆቹ ሲቀላቀል፤በጉዲፈቻ /በማደጎ የተወሰደ ) የመሳሰሉት ለውጦች ሲኖሩ ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት አባሉ በወቅቱ መረጃ በማቅረብ ማህበሩ ጽሕፈት ቤት ቀርቦ አዲስ ቅጽ መሙላትና ማስተካከል ይጠበቅበታል። ላልተመዘገበ ሰውና ላልተስተካከለ ምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ አይሰጥም።

## አንቀጽ ስምንት፦ የአባል መብት ፦

8፡1የማህበሩ የገንዘብ አቅም እንደፈቀደ፤ የማህበሩ አባል፤ ሚስት፤18 አመት ዕድሜ ያልበለጠ ልጅ (የኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆኖ በቤተሰብ ሥር የሚኖር እድሜው ከ23 ዓመት ያልበለጠ ) ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ፤ ለቀብር ማስፈፀሚያ ወይም ወደ ሀገር ቤት አስከሬን ለመላኪያ የሚሆን የማህበሩ ተቀማጭ ገንዘብ አቅም እንደ ፈቀደ እስከ.. ....$10,000.00(አስር ሺ ዶላር) ድረስ ለሚች ቤተሰብ አባል ወይም በቤተሰብ ስምምነት ለሚወከለው ሰው ፣ ወይም ቀድሞ በኑዛዜ ለተወከለ ሰው ይሰጣል።

8:2 የማህበሩ ተቀማጭ ገንዘብ 50,000 ብር ደርሶ መቅበር የሚያስችል ደረጃ በታች እንዳይሆን የእድሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሰረት እያንዳንዱ አባል ተጨማሪ መዋጮ ይከፍላል ።

**ማሳሰቢያ ፦ የሚከፈለው የገንዘብ መጠን የሚውሰነው በወቅቱ ባለው በአባላት ብዛትና በማህበሩ የገንዘብ አቅም ላይ ተመስርቶ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል።**

8:3 አንድ የማህበሩ አባል በሥራ ወይም በሌሎች ምክንያቶች ከኮሎራዶ ስቴት ወጭ ወደ ሌላ ስቴት ቢዛወር፤ወይም ወደ ሀገር ቤት (ኢትዮጵያ) ሄዶ ቢኖርና በእርሱም ሆነ በተመዘገቡ ቤተሰቦቹ (ችዋ) ላይ የሞት አደጋ ቢደርስ፤የማህበሩን ደንብና ህግ ጠብቆ ወርሃዊና ሌላም ማህበሩ የሚጠይቀውን መዋጮ በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት በወቅቱ እስከ ከፈለ ድረስ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ሙብቱ ተጠብቆ የሞት አደጋው በደረስ 24 ሰአት ውስጥ ለማህበሩ አመራር በጽሁፍ (በኢሜል፤ በቴክስት) ሲያስታውቅና ህጋዊ የሞት ማስረጃ ሲያቀርብ ይከፈለዋል።

8፡.4 በማጭበርበር የእድሩን ገንዘብ የወሰደ አባል በህግ ተጠያቂ ይሆናል ።የውሰደውንም የማህበሩን ገንዘብ ከነወለዱ ፣ለጠበቃና ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተደረጉ ሌሎች ወጪዎችንም ጨምሮ ይከፍላል, እንዲሁም ከእድሩ ይሰናበታል::

8፡5 ማንኛዉም የማህበሩ አባል የመመረጥ ፤የመምረጥ፤ በተለያዩ የማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ ፣ገንቢ ሀሳብ የማቅረብ ዲሞክራሲዊ ሙብቱ የተጠበቀ ነው።

አንቀጽ ዘጠኝ ፦አገልግሎት ለማግኘት የመቆያጊዜ(grace period) ፦

አንድ ሰው የማህበሩ አባል ለመሆን ቅጽ ሞልቶ የመመዝገቢያና የ6 ወሩን ወርሃዊ ክፊያ በቅድሚያ ከከፈለ በኋላ ከማህበሩ የአገልግሎት ክፍያ የሚያገኘው ስድስት (6) ወሩን ከአጠናቀቀ በኋላ ይሆናል ።

አንቀጽ አሥር፦ከእድሩ ስለመሰናበት፦

10:1 አንድ አባል በየስድስት ወሩ የሚከፈለውን የማህበሩን ወርሃዊ መዎጮ በሶስት ወር ውስጥ ካልካፈል በኢሜልና በቴክስት ጽሁፍ እንድሁም በስልክ ማሳሰቢያ ከማህበሩ ይሰጠዋል። በከባድ ህመምና ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች በማስረጃ ካልተረጋገጠ በስተቀር በዚህ 3 ወር ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ካልከፈለ ፤ በ4ኛው ወር 15%፤በ5ኛው ወር 20% እና በ6ኛው ወር 30 % ቅጣቱን ጨምሮ ካልከፈለ ከማህበሩ በፈቃዱ እንደተሰናበተ ተቆጥሮ ይሰረዛል።

10:2 አንድ አባል የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ባለማክበር በሥነስርአት ጉድለት ተገቢው ምክርና ተግሳጽ በቃልና በጽሁፍ ተሰጥቶት ከድርጊቱ መመለስ ካልቻለ የእድሩ መተዳደርያ ደንብ በሚያዘው ውሣኔ መሠረት ከእድሩ ይሰንበታል።

10:3 አንድ አባል የማህበሩ አባል ሆኖ መቀጠል ካልፈለገ በጽሁፍ አቅርቦ ከማህበሩ በራሱ ፍላጎት መሰናበት ይችላል።

10:4 አንድ አባል በማንኛውም ሁኔታ ከማበሩ ከተሰናበተ ቀደም ብሎ የከፈለው ማንኛውም ገንዘብ አይመለስለትም።

10:5 በራሳቸው ወይንም በጥፋት ከእድሩ ተሰናብተው እንደገነ ወደ እድሩ መመለስ ለሚፍልግ አዲስ የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ የእድሩ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድከተወሰነ በኋላ እንደ  አዲስ ተመዝግቦ የመመዝገቢያ ክፍያና የ6 ወር ወርሃዊ መዋጮ በመክፈል አባል መሆን ይችላል። የ6 ወር የመቆያ ጊዜም ተግባራዊ ይሆናል።

## አንቀጽ አስራአንድ ፦የማህበሩ (እድሩ) አመራር መዋቅር

ማህበሩ(እድሩ) ቀጥሎ የተመለከተውን መዋቅር ይኖረዋል።  የእድሩ ተጠሪነት  ለጠቅላላ ጉባኤና ለኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ፤ (አሰራሩ በሚወጣው የሥራ ደንብ ይወሰናል) :: የማህበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ  ፤ እና የቁጥጥር (ኦዲት ) ኮሚቴ የተዋቀረ ነው።

11.1 ጠቅላላ ጉባኤ ፦

ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ፦ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛው የማህበሩ አባላት የሚሳተፉበት ጠቅላላ ስብሰባ ሲሆን ፤ የማህበሩ   ከፍተኛና የመጨረሻ ወሳኝ አካል ነው።

11:2 ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ በየዓመቱ በጥር ወር (January) ያደርጋል።

የጠቅላላ ጉባኤን ውሳኔ የሚጠይቁ አስቸኳይ ጉዳይ ሲኖር ፤በሥራ አስፈጻሚ ቦርድና ፤ በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ አሰራሩ በሚወጣው የየሥራ ደንብ ይወሰናል; የጋራ ስብሰባ በ2/3ኛ ድምጽ እንዲጠራ ከተጠየቀ በማንኛውም ጊዜ ከዓመት ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል ።

11:3 የጠቅላላ ጉባኤ የሥራ ኃላፊነት ፦

11:3:1በአስመራጭ ኮሚቴ የሚቀርብለትን የማህበሩን የስራ አስፈጻሚ ኮሙቴ አባላትን ፤ይሾማል፤ይሽራል

11:3.2 በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ የማህበሩ የበላይ ጠባቂና አማካሪ ሆኖ እንዲሰራ ዕውቅና (confirmation) ይሰጣል ።

11.3.4 የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል

11.3.5 የቀጥጥርና ኦዲት ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል

11.3.6የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብን ያፀድቃል፤ ያሻሽላል፤ይሽራል

11.3.7 የማህበሩን የሥራ ማስኬጃ ባጀትና እቅዶችን ያፀድቃል።

11.3.8 በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤ በኮሎራዶ የኢትዮጵያውያን ኮሙኒቲና በቁጥጥር ኮሚቴ የሚቀርብለትን አመታዊ ሪፖርት ያዳምጣል ፤ይመረምራል፤እንዲጣራ ያደርጋል፤እንድ አስፈላጊነቱም የእርምት መመሪያዎችን ይሰጣል።

11.3.9 የማህበሩ ሂሳብ በውጭ መርማሪዎች (ኦዲተሮች)እንዲመረመሩ መመሪያ ይሰጣል ።

11.3.10 የማህበሩ ተቀማጭ ገንዘብ አምስት (5) አስከሬን መቅበር ከሚያስችል ደረጃ በታች እንዳይወርድ አባላት ተጨማሪ መዋጮ እንዲያዋጡ ይወስናል።

11.3.11 በጠቅላላ ጉባኤ በሚወሰነው መሰረት አሁን ያለው የመመዝገቢያና ወርሃዊ መዋጮ በየጊዜው እየታየ አሁን ባለው ላይ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።

## አንቀጽ አስራ ሁለት፦ የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ምልአተ ጉባኤ (ኮረም)፦

12.1 ከግማሽ በላይ የማህበሩ አባላት የተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤው እንደተሟላ ተቆጥሮ ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል ።
ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምልአተ ጉባኤው ካልተሟላ ፤ በቀረበው አጀንዳ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጎበት፣በቂ ጊዜና ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ተከታይ ሁለተኛ ስብሰባ ይጠራል።
አሁንም በሁለተኛ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤው ካልተሟላ ፣ ስብሰባው ምልዓተጉባኤው እንደተሟላ ተቆጥሮ በተገኙት አባላት ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላል። ውሳኔውም በሁሉም የማህበሩ አባላት ላይ የፀና ሆኖ ሥራ ላይ ይውላል ።

12.2 ስብሰባ ላይ ስለመገኘት

ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ መገኘት ግዴታ ነው። ያለበቂ ምክንያት በስብሰባው ያልተገኘ አባል $10.00 ቅጣት ይከፍላል ።

12.3 ውክልና ስለመስጠት

ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በስብሰባው ላይ መገኘት የማይችል ፤ከኮሎራዶ ስቴት ውጭ በሌላ ስቴት ወይም በሌላ ሀገር(ኢትዮጵያን ጭምሮ) የሚኖር የማህበሩ አባል በሚደረገው በማንኛውም የማህበሩ ስብሰባ ላይ እሱን ወክሎ የሚገኝ፤እንደራሱ ሆኖ ድምጽ የሚሰጥ ፤ የማህበሩ ህገደንብ የሚይጥይቀውን ማንኛውንም እንደራሱ ሆኖ የሚፈጽምለትን ከማህበሩ አባላት መካከል አንድ ሰው ወይም የቅርብ ቤተሰቡን አንድ ሰው በጽሁፍ መወከል ይችላል።

አንቀጽ አስራ ሶስት፦በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ (አሰራሩ በሚወጣው የሥራ ደንብ ይወሰናል) ኃላፊነት ፦

13.1 ከማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው ኃላፊነት መሰረት የማህበሩ የበላይ ተመልካች በመሆን በየሶስት ወር አንድ ጊዜ ከማህበሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጋር የጋራ ስብሰባ በማድረግ የሥራ እንቅስቃሴንና የፋይናንስ አያያዝን ይገመግማል፤እንደአስፈላጊነቱ ተገቢ ምክርና አስተዳደራዊ መመሪያ ይሰጣል ።

በአጠቃላይ የህዝብ ተወካይ እንደመሆኑ መጠን የማህበሩ ህልውና እንዲጠበቅ ከበላይ ሆኖ እንቅስቃሴውን ይከታተላል ፤ ደካማ አሰራሮች በውቅቱ እንዲታረሙ ፤አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በውይይት እንዲፈቱ ይመክራል ፤ የአስታራቂነት ሚና ያከናውናል ፤ እምቢተኞችን ይገስጻል ውጤቱንም ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት አቅርቦ ያስወስናል።

13.2 የኮሎራዶ ኢትዮጵያን ኮሙኒቲ (አሰራሩ በሚወጣው የሥራ ደንብ ይወሰናል) በማህበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የእለት ተእለት የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ አይገባም።

## አንቀጽ አስራ አራት፦የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

14.1 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአስመራጭ ኮሚቴ ተመርጠው ለጠቅላላው ጉባኤ ቀርበው የሚፀድቁ ከ7 እስከ 9 አባላት ያሉት ይሆናሉ።

ዝርዝራቸውም ፦
አንድ የማህበሩ ሊቀመንበር ፤
አንድ ምክትል ሊቀመንበር ፤አንድ ጸሐፊ ፤
አንድ ምክትል ጸሐፊ አንድ ገንዘብ ተያዥ፤
አንድ ረዳት ገንዘብ ያዥ ፤
አንድ የሂሳብ የሹም(አካውንታንት)፤
ሁለት የማህበራዊና የህዝብ ግነኙነት ኃላፊዎች ይሆናሉ።

14.2 የአገልግሎት የስራ ዘመናቸው 3 ሶስት ዓመት ይሆናል።
አንድ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በህዝብ ፍላጎት ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል። ሆኖም ከሁለት የአገልግሎት ዘመን(ተርም) በላይ መመረጥ አይችሉም ።

14.3 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የወል ኃላፊነት ፦

1.የማህበሩ ህገ ደንብ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ
2.የማህበሩ ገቢ በወቅቱ መሰብሰቡንና በማህበሩ የባንክ አካውንት ገቢ መደረጉን በሂሳብ ሹሙ በየወሩ በሚቀርበው ሪፖርት ማረጋገጥ ።
ወጪዎች በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት መከናውናቸውን፤ለቀብር የሚሰጡ እርዳታዎች በደንቡ መሰረት በወቅቱ መከፈላቸውን ማረጋገጥ
3. የማህበሩ ንብረትና ገንዘብ በአግባቡ መያዙን ማረጋገጥ
4.በአጠቃላይ የማህበሩ ህልውና ተጠብቆና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያላሰለሰ የጋራ ጥረት ማድረግ ይሆናል ።

አንቀጽ 15 ፦ዝርዝር የስራ ኃላፊነት ፦

- ሀ/ የማህበሩ ሊቀመንበር የሥራ ኃላፊነት ፦

15.1 የማህበሩ የሥራ አመራር ሊቀመንበር በምርጫ ኮሚቲ ተመርጠው ከሚቀርቡት መካከል በድምጽ ብልጫ በጠቅላላው ጉባኤ ይመርጣል ። የአገልግሎት ዘመኑ 3 ሶስት ዓመት ይሆናል ። በአባላቱ ድምጽ ብልጫ ለሁለተኛጊዜ ሊመረጥ ይችላል ። ሆኖም ከሁለት የአገልግሎት ዘመን በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል ።
.በማህበሩ የሥራ አመራር ኃላፊነት ላይ በየዘርፉ በስሩ የተመደቡት የአመራር አካላት ስራቸውን በደንቡ መሰረት መስራታቸውን ይቆጣጠራል።እንዲሁም ለሌሎች የስራ ባልደረቦቹ መልካም አርአያ በመሆን አመራር ይሰጣል ።

15.2 ማህበሩን በመወከል በውስጥም ሆነ በውጭ ለማህበሩ ጠቃሚ ጉዳዮችን ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ይነጋገራል ፤ ለማህበሩ ጠቃሚ የሆኑ ስምምነቶች ይፈርማል።

15.3 የጠቅላላ ጉባኤውን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል ፤ስብሰባውንም ይመራል። የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል።

15.4.ከኮሎራዶ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ (አሰራሩ በሚወጣው የሥራ ደንብ ይወሰናል) እና የሥራ አስፈጻሚ ጋር በየሦስት ወሩ በሚደረገው የጋራ ስብሰባ ላይ የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል።ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውን በጀትና የሥራ ዕቅዶችን አቅርቦ በጋራ ይወሰናል።

15.5.በማንኛውም የማህበሩ የባንክ ሂሳብ የወጪ ቼኮች ላይ ከሂሳብ ሹም ጋር በመሆን በጥምር ይፈርማል።

15.6 የማህበሩ የገንዘብ ወጪዎች በህገደንቡ መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ክፊያ እንዲፈጸም ያዛል።

- ለ/ የማህበሩ ምክትል ሊቀመንበር የሥራ ኃላፊነት፦የማህበሩ ሊቀመንበር በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል ።
- ሐ/ ጸሐፊ/ም.ጸሐፊ
- መ/ ገንዘብ ያዥ/ረዳት ገንዘብ ያዥ
- ሠ/ ሂሣብ ሹም
- ረ/ ቁጥጥር /ኦዲት ኮሚቴ

15.7 የቁጥጥርና ኦዲት ኮሚቴ የሥራ ኃላፊነት

## አንቀጽ አስራ ስድስት(16) ፦የማህበሩ ምክትል ሊቀመንበር የሥራ ኃላፊነት ፦

16.1 የማህበሩ የስራ አመራር ምክትል ሊቀመንበር በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ ለ3 አመት የሥራ ዘመን ይመረጣል፤ለሁለተኛ ጊዜ በአባላት ድምጽ ካገኘና ፈቃደኛ ከሆነ ሊመረጥ ይችላል ፤ ተጠሪነቱ ለስራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል ።
የምክትል ሊቀመንበሩ የስራ ድርሻና ኃላፊነት የሚከተሉት ናቸው

16.2 የማህበሩ ሊቀመንበር በማይኖርበት ወቅት እሱን ተክቶ ኃላፊነቱን በመውሰድ ማህበሩን ይመራል፤ከሂሳብ ሹም ጋር በመሆን የወጪ ቼኮችን ይፈርማል፤ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰርት አስፈላጊ ወጪዎችን ያዛል፤መፈጸማቸውንም ይከታተላል።

16.3.በማንኛውም የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ ሊቀመንበሩን ይረዳል፤ በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ተጨማሪ ስራዎች ፤የበአል ዝግጅቶችን፤ንኡሳን ኮሚቴዎችን የማቅዋቋምና የመምራት የመሳሰሉትን ይሰራል ፡፡

16.4 በስብሰባ ወቅት የማህበሩ ዋና ጸሐፊና ረዳት በማይኖሩበት ጊዜ የጸሐፊነትን ስራ ይሰራል ፡፡ ሊቀመንበሩ፤ ጸሀፊውና ረዳት በአንድ ጊዜ በማይኖሩበት ወቅት ምክትል ሊቀመንበሩ ስብሰባውን ይመራል፤ በጊዜያዊ ጸሐፊነት የሚያገለግለውን ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ አንዱን ይመድባል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት(17)፦የማህበሩ ዋና ጸሐፊ የስራ ኃላፊነት ፦

17.1 የማህበሩ ዋና ጸሐፊ በጠቅላላ ጉባኤ ለ3 አመት አገልግሎት ይመረጣል ፤ለሁለተኛ ጊዜ በጉባኤው ድምጽ ሊመረጥ ይችላል ፡፡ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡
ዋና ጸሐፊው የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

17.2 የማህበሩን ማንኛውንም ጽሑፍ ነክ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፤ ይቆጣጠራል፤ይንከባከባል፤ምስጥርነታቸውን ይጠብቃል

17.3 የማህበሩን አባሎች ግል ማህደር በአግባቡ በኤሌክትሮኒክስ(ኮምፒውተር) እና በወረቀት ሰነድነት ይይዛል፤ምስጥርነታቸውንም ይጠብቃል ፤የአባሎችን አድራሻና ዝርዝር መረጃ ይመዘግባል፤

17.4 ከማህበሩ ሊቀመንበር እሱ በሌለበት ከምክትል ሊቀመንበሩ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን፤የስብሰባ ቦታና ሰአት ይወስናል ፤ የስብሰባ ጥሪዎችን በወቅቱ ያስተላልፋል፤ በስብሰባ ወቅት ቃለጉባኤዎችን ይይዛል፤በስብሰባ ላይ የተገኙትን አስፈርሞ በፋይል ይይዛል፤ የስብሰባ ኮረም መሙላቱን፤የድምጽ አሰጣጥ በአግባቡ መሆኑን ያረጋግጣል፤

17.5 ሊቀመንበሩ እና ምክትል ሊቀመንበሩ በማይኖቡት ወቅት እነሱን ተክቶ እንደ ሊቀመንበር ሆኖ ይሰራል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት(18) ፦የረዳት ጸሐፊ የስራ ኃላፊነት

18.1 ዋና ጸሐፊ በማይኖርበት ወቅት እሱን ተክቶ የጸሃፊነቱን ስራ ይሰራል፡፡

18.2 በዋና ጸሐፊው የሚሰጠውን ማንኛውንም የጽሕፈት ስራ ይሰራል ፡፡ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ (19) ፦የማህበሩ ገንዘብ ያዥ የስራ ኃላፊነት ፦

የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባኤ ለ3 አመት ይመረጣል ፤በጉባዔው ለሁለተኛ ተከታታይ ሊመረጥ ይችላል ፤ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ይሆናል።

የገንዘብ ያዥ የስራ ኃላፊነት የሚከተሉት ይሆናሉ፦

19.1 ማንኛውንም የማህበሩን ገቢ ህጋዊ ደረሰኝ በመስጠት ይሰበስባል። የተሰበሰበውን የማህበሩን ገንዘብ በ24 ሰአት ጊዜ ውስጥ በማህበሩ ስም በተከፈተው የባንክ አካውንት ያስገባል፤ገቢ ያደረገበትን የባንክ ደረሰኝ ተቀብሎ በጥንቃቄ ይይዛል።
በሊቀመንበሩ ወይም እሱ ከሌለ በምክትል ሊቀመንበሩ ሲታዘዝ ወጪዎችን ይፈጽማል፤የወጪ ደረሰኞንም ተቀብሎ በአግባቡ ይይዛል።
የወጪና የገቢ ደረሰኞችንና ተያያዥ ሰነዶችን ከማህበሩ ሂሳብ ሹም (አካውንታንት)እና ኦዲተር ጋር በመተባበር ያስመዘግባል፤ያስመረምራል።

## አንቀጽ ሃያ (20) ፦የሂሳብ ሹም የስራ ኃላፊነት ፦

የማህበሩ ሂሳብ ሹም ለ3 አመት የስራ ዘመን በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል ። ለተከታታይ ሁለተኛ የስራ ዘመን ሊመረጥ ይችላል ። ተጠሪነቱ ለስራአስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል ።የሂሳብ ባለሙያ ቢሆን ይመረጣል

ሂሳብ ሹሙ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የስራ ሃላፊነት ይኖረዋል፦

20.1 የማህበሩን የሂሳብ አያያዝ ግልጽና ዘመናዊ የአሰራር ሲስቴም ይዘረጋል ።

20.2 የማህበሩን የወጪና ገቢ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ይቆጣጠራል፤ ደረሰኞችን ያሳትማል፤በአግባብ ይይዛል፤ለሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑትን ለገንዘብ ያዡ መዝግቦ ይሰጣል።

20.3 ወጪ የተደረገባቸውን ሰነዶችንና ደረሰኞችን ከገንዘብ ያዥ ተቀብሎ ትክክለኝነታቸውን ያረጋግጣል፤በሂሳብ መዝገብ (ሌጀር) ይመዘግባል።

20.4 ከማህበሩ ሊቀመንበር ጋር ፤እሱ በሌለበት ወቅት ከምክትል ሊቀመንበሩ ጋር በመሆን የወጪ ቼኮችን ትክክለኝነት በማረጋገጥ በጥምር ይፈርማል።

20.5 የማህበሩ የባንክ አካውንት ሲከፈትም ሆነ ሲዘጋ ከሊቀመንበሩ ጋር በመሆን ይፈርማል።

20.6 የማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ በየስድስት ወሩ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፤ እንዲሁም በየዓመቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎችና እንደአስፈላጊነቱ የሂሳብ ሪፖርት ያቀርባል።

20.7 የማህበሩን ሂሳብ በኦዲተር ያስመረምራል፤አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በውጭ ኦዲተር ያስመረምራል። በአጠቃላይ የማህበሩ የገንዘብ እንቅስቃሴ ግልጽነት (transparency) ባለው ሁኔታ መሆኑን ያረጋግጣል

## አንቀጽ 21 የቁጥጥር (የኦዲት) ኮሚቴ የስራ ኃላፊነት ፦

የማህበሩ ቁጥጥር ሶስት አባሎች ያሉት ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤ ለ3 አመት የስራ ዘመን ይመረጣሉ።ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ። ተጠሪነታቸው ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል ። ተመራጮች የሂሳብ ባለሙያና የኦዲት ልምድ ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል ። የቁጥጥር ኮሚቴ
የስራ ኃላፊነት የሚከተሉት ይሆናሉ፦

21.1 ማንኛውንም የማህበሩን የገንዘብ አስተዳደር ፤ አያያዝ፤የወጪና የገቢ እንቅስቃሴ ይመረምራል፤የማህበሩ ህገደንብ በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል ፤ ከአድሎና ሙስናያ የፀዳ ፤ግልጽነት ያለው አስተዳደር መሆኑን ያረጋግጣል ፤የተገኘውንም የምርመራ ውጤት ከእርምት አስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ በሪፖርት ያቀርባል።

21.2 በየስድስት ወር የሂስብና አስተዳደር ሪፖርት ለስራ አመራር አካላት በሚደረገው ስብሰባ ያቀርባል፤ደካማ አሰራሮች እንዲታረሙ አስተያየት ይሰጣል ።

21.3 በማንኛውም ጊዜ የማህበሩን የሂሳብ መረጃዎችን ፤ፋይሎችን፤ የባንክ ገቢና ወጪዎችን በሰነድና በኮምፒውተር ያለውን በፈለገ ጊዜ ማየትና መመርመር ይችላል ።

21.4 የማህበሩ የስራ አመራር የስራ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የሂሳብ በቁጥጥር በማድረግ በነባሮቹ አመራር የተካሄደውን የገንዘብ ወጪና ገቢ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል።

## አንቀጽ 22 ፦የአስመራጭ ኮሚቴ የሥራ ኃላፊነት

22.1 ሶስት( 3) አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ በኮሙኒቲው የባለአደራ ቦርድና በሥራ አስፈጻሚ ቦርድ በጋራ ስብሰባ ይመረጣሉ

22.2 አስመራጭ ኮሚቴው ከየእምነት ተቋማት በሁለቱ ቦርዶች የተጠቆሙትን እጩዎች ባለው መመዘኛ መሰረት ሙያቸውንና የስራ ልምዳቸውን በመመርመር በየስራ መስኩ ይመድባቸዋል።

22.3 አስመራጭ ኮሙኒቲው የእያንዳንዱን  እጩ ተመራጮች አጠር ያለ የስራ ልምድ፤እውቀትና ማህበራዊ ታሪካቸውን ለጠቅላላ ጉባኤ ይገልጻል።

22.4 በየስራ መስኩ የመደባቸውን እጩ ተመራጮች ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስፀድቃል።

22.5 ከየእምነት ተቋማት አንዳንድ ሰው በማህበሩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ መመረጡን ያረጋግጣል።

22.6 የተመረጡት አባላት ለተመረጡበት የስራ ኃላፊነት ህብረተሰቡን በቅንነት ለማገልገል ቃል መግባታቸውን ያረጋግጣል።

22.7 ያልተመረጡት በየእምነት ተቋማቸው ተመልሰው በተጠባባቂነትና በንዑስ ኮሚቴነት እንዲሰሩ ይሰይማቸዋል።

22.8 ምርጭው በትክክል መካሄዱን ያረጋግጣል። የምርጫ ሰነዶች በጥንቃቄ በጽህፈት ቤቱ እንዲቀመጡ ለህዝብ መማክርት አሰረክቦ በምስጋና ይሰናበታል።